# ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ

## ትዕይንት አንድ

1. ከአቶ አበጀ መኖሪያ ቤት

1.1 ከቤቱ በረንዳ ላይ እና ከግቢው ውስጥ

1.1.1 የግቢው በር ከውስጥ እየታየ

ፍሬው - በወጣቶች እድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን/ የግቢውን በር ከውስጥ ከፍቶ ይገባና መለስ ብሎ የግቢውን በር ይዘጋዋል። በእጆቹ መጽሐፍ ይዟል።

1.2 ከቤቱ በረንዳ ላይ

1.2.1 የግቢውን በር ሲዘጋ በመታከክ የሳሎኑን በር ሲከፍት ይታያል።

አቶ አበጀ - የሳሎኑን በር ከፍተው ይወጡና ሊዘጉት ሲሉ ልጃቸው ወደ እሳቸው መምጣቱን ሲመለከቱ ሊዘጉት ያሉትን በር ትተው ወደ ፍሬው ዞረው ያናግሩታል።

ፍሬው - እየተጣደፈ በመራመድ መጥቶ ከበረንዳው ሲደርስ ቆም ብሎ ከአባቱ ጋር ከተነጋገረ በኋላ አልፏቸው አባቱ በወጡበት በር ገብቶ በሩን ከውስጥ ይዘጋውና ይሰወራል።

አቶ አበጀ - ፍሬውን ካነጋገሩት በኋላ ከዘራቸውን ከግድግዳው ላይ አስደግፈው ከላይ ከለበሱት ላይ የደረቡትን ጋቢያቸውን ገለጥለጥ አድርገው እንደ ገና እያጣፉ አስተካክለው ከለበሱት በኋላ የራሳቸውንም ባርኔጣ ያስተካክሉና ከዘራቸውን አንስተው እየተጣደፉ ከበረንዳው ወርደው ወደ ግቢው በር ማምራት እንደ ጀመሩ አቋርጧቸው ከሳሎኑ ውስጥ የፍሬው እና የቤት ሠራተኛው የበላይነሽ ጠብ አዘል ንትርክ ይሰማል።

አቶ አበጀ - ደንገጥ ብለው በደረሱበት ይቆሙና ወደ ሳሎኑ በር ዞረው ጆራቸውን ቀስረው ያዳምጣሉ። ንትርኩ እየበረታ ሲሄድ እየተጣደፉ ወደ መጡበት ይሄዱና የሳሎኑን በር ከፍተው ገብተው ይሰወራሉ።

# ትዕይንት ሁለት

2. ከሳሎኑ ውስጥ

2.1 ሦስቱም ከሳሎኑ ውስጥ ቆመዋል

አቶ አበጀ - ወደ ሰፋው ወንበር ዞረው እየሄዱ በመቃወም አ.አ.አ--

አይደለማ የኔ ልጅ ምን ነካብኝ ዛሬ !

ፍሬው - እንዴት ጭራሽ እኔን እንደ ጥፋተኛ ልትቆጣኝ?!

አበጀ - እየተቀመጡ ጥፋተኛ ነህ ብዬ ለመውቀስም ባይሆን ይህ አሁን የምትጣሉበትን ነገር እንደ ሰማሁት ከሆነ “ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ” እንደሚባለው ተረት ያለ ነው።

ፍሬው - እራሱን እየያዘ አቤት አባዬ ደግሞ ወደ ሠራተኛዋ እየጠቆመ እኛ ስለሚበላ ነገር እያወራን አንተ ሰለ ላምና ስለ ኩበት ትናገራለህ።

አበጀ - “ ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ” እየተባለ ወንበሮቹን እየጠቆሙ እስቲ መጀመሪያ ቁጭ በሉና ተሳስቼም ከሆነ እታረማለሁ።

/ ፍሬው እና በላይነሽ ይቀመጣሉ።/

አበጀ - እ.ሺ በሉ.ያ -- የጠባችሁን መንስኤ ንገሩኛ

ፍሬው - ይኸውልህ አባዬ ገና ከጥዋቱ ወደ ሥራ ስሄድ ከሰዓት በኋላ አንድ ጓደኛዬን ከዚህ ቤት ስለ ቀጠርኩት ለምሳ የምታዘጋጅው ምንድን ነው አልኳት ። ሽሮ ቤት አለኝ።

በላይነሽ - አቋርጣው እና ሽሮ ከሆነ ...

አበጀ - አቋርጠዋት ቆይ አንቺ -- ጨርስ አንተ

ፍሬው - ከዛ በኋላ ለጓደኛዬ ሽሮ ከምንጋብዘው አልኩና ሰላሳ ብር ቆጥሬ ከሰጠኋት በኋላ

ሌላ ነገር ግዢና አዘጋጅተሽ ጠብቂኝ አልኳት።

ወደ ጓዲያው በንዴት እየጠቆመ - እንቁላልና ቲማቲም ብቻ ገዝታ ስታበቃ ...

አበጀ - ወደ በላይነሽ ዞረው እያዩ እንቁላልና ቲማቲም?!

በላይነሽ - እንቁላልና ቲማቲም ብቻ ሳይሆን አባባ ከዚህ ከቤት ከጨመርኳቸው ዘይትና

ሽንኩርት ጋር ከመሳሰሉት ነገሮች በተጨማሪ በሰጠኝ ሰላሳ ብር መግዛት

የምችላቸውን ነገሮች ሁሉ ገዝቻለሁ።

ፍሬው - ቆጣ ብሎ በመመናጨቅ እና ይሄን ሁሉ ትርኪምርኪ ገዝተሽ ከምትጠብቂኝ

ቢያንስ ግማሽ ኪሎ ሥጋ ገዝተሽ ወጥ ነገር ሰርተሽ ብትጠብቂኝ አይገባም ነበር!?

አበጀ - ቢሊው! ግማሽ ኪሎ ሥጋ?

በላይነሽ - የውሎት እንግዲህ

አበጀ - እሺ በሰላሳ ብር...

ፍሬው - በርጋታ ምን ለወጥ የሚሆን ሥጋ?

አበጀ - እና ቢሆንስ?! ነው ወይስ የበሬም ሳልቫጅ አለው ልትለኝ?!

በላይነሽ - ትስቃለች

ፍሬው - እያፈጠጠባት ደ.ደ.ደግሞ ትስቂያለሽ እንዴ?

አበጀ - እየሳቁ - ብትስቅስ! አ.ህ እኔ እሺ ስማ መጀመሪያውንም ቢሆን አልሰማህም አልከኝ

እንጂ ሰላሳ ብር ከሰጠሃት በኋላ ለምን የሰማንያ ብር ምሳ አልበላሽም ብለህ

መጣላትህን እንጃየሁ እንዲህ ዓይነቱ ነገር ማለት “ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ”

የሚለውን የአባቶች ተረት ይወክላልና / የግቢው በር ሲንኳኳ ይሰማል ሠራተኛዋ

ወደ ውጪ ዞር ብላ ታያለች/ ጥፋተኛነትህን አምነህ ይቅርታ ጠይቃት

ብዬህ ነበርና አሁንም ይህ ጓደኛህ እየመጣ ስለሆነ ተነስተህ ይቅርታ ጠይቃት።